

# ስለ እሳት አደጋ ጥንቃቄዎች ይጨዋወቱ

ከሌሎች ጋር ሲነጻጸር በእድሜ ከ 70 በላይ የሆኑ ሰዎች በአራት እና በአምስት እጥፍ በእሳት አደጋ ይሞታሉ፡፡ በጥቂቱ በቀላሉ በሚወሰዱ እርምጃዎች የምታስቡላቸውን አረጋውያኖች ለእሳት የመጋለጥ አደጋን መቀነስ ይችላሉ፡፡ ስለ ጥንቃቄ፣ በቤት ውስጥ የሚከሰቱ አደጋዎችን ስለማወቅ እና የእሳት አደጋን ለመቀነስ ምን ማድረግ ስለሚገባዎት ነገሮች ጠቃሚ የሆነ ውይይቶችን ያድርጉ፡፡

## ስለ እሳት አደጋ በሚጫወቱበት ወቅት፤ ስለሚከተሉት መወያየት አለብዎ

- በማድቤት ውስጥ ስለሚደረግ የእሳት አደጋ ጥንቃቄ እና የምግብ አዘገጃጀት
- የኤሌክትሪክ እቃዎችን በአግባቡ ስለመጠቀም
- የማስጠንቀቂያ ደወል እና የማምለጫ መስመሮች
- እሳት እንዴት እንደሚጠፋ
- ስለ ሻማዎች እና ማጨስ

ጓደኛ ወይም ዘመድ ከሆኑ ይህንን በጣም ጠቃሚ የሆኑ እሳት አደጋ መከላከያ እርምጃዎችን የያዘ መመሪያ አዘጋጅተንልዎታል፡፡

## እንደ ጓደኛ ወይም እንደ ዘመድ በሚከተሉት መርዳት ይችላሉ

- የምድጃ መከላከያ በመትከል
- ከምድጃው በላይ ያለውን የንፋስ ማራገቢያ ማጣሪያ ማጽዳት
- የጭስ ማስጠንቀቂያ ደውሉ እንደሚሰራ እንዲሁም በሙሉ ቤት ውስጥ እንደሚሰማ ማረጋገጥ
- ነዋሪው ሊጠቀመው የሚችለው እሳት ማጥፊያ እንዳለ ማረጋገጥ
- ነዋሪው እሳት አደጋን መከላከልን ያማከለ የማጨስ ልምድ እንዲኖረው ማረጋገጥ
- መጋረጃዎች፣ልብሶች፣ ጋዜጣዎች እንዲሁም የእንጨት ቁሳቁሶች ከኤሌክትሪክ የግድግዳ ማሞቂያዎች ጋር ርቀታቸውን ጠብቀው እንደተቀመጡ ማረጋገጥ
- አደገኛ የሆኑ መብራት ማቀፊያዎችን፣ የማጌጫ መብራቶችን እና ቋሚ ያልሆኑ ሻማዎችን ማስወገድ

በ sikkerhverdag.no ለአረጋውያን ስለሚገቡ የእሳት አደጋ ጥንቃቄዎችን በበለጠ ማንበብ ይችላሉ፡፡

ALT VI KAN MOT BRANN

ስለ እሳት አደጋ ውይይት ማድረግ የ'Alt vi kan mot brann' አካል ሲሆን እስከ 2020 የሚደረግ በእሳት አደጋ መከላከል ላይ የሚደረግ መነሳሳት እና ውይይት ነው፡፡ ይህ ተነሻሽነት የተቀናጀው ከ DSB በተሰራው National Coordination Group for Fire Communication (ሀገር አቀፍ እሳት አደጋ መከላከያ ቅንጅት የውይይጥ ቡድን) ፣ ከ Norwegian Association (ከኖርዌዎች እሳት መከላከያ ባለስልጣናት ማህበር)፣ ከ Norwegian Association of Chimney Sweeps (Feiermesternes landsforening) )(የኖርዌዬች ጭስ ማውጫ መጥረጊያ ማህበር)፣ ከ Norwegian Fire Information Forum (Branninformasjonsforum) )(የኖርዌዬች የእሳት አደጋ መረጃ ፎረም)፣ ከ Local Electrical Safety Inspection Authorities (DLE)(የአከባቢው የኤሌክትሪክ ጥንቃቄዎች ምርመራ ባለ ስልጣን)፣ ከ the Register of Competent Companies (Sakkyndigeselskap) (የተመዘገቡ ተፎካካሪ ድርጅቶች), NELFO, Finance Norway(የኖርዌይ መዋለ ንዋይ)፣ and the Norwegian Fire Protection Association (የኖርዌይ እሳት አደጋ ጥበቃ ማህበር) ነው፡፡ ቡድኑ በ DSB የሚመራ ነው፡፡ የአከባቢው የእሳት አደጋ መከላከል ክፍል ፣ የጭስ ማስወገጃ አገልግሎት እና በአጠቃላይ በሀገሪቷ ያለው የኤሌክትሪክ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን በየአከባቢው ስለሚካሂደው የፕሮግራሙ መነሳሳት ሀላፊነት ይወስዳል፡፡

## ምድጃዎን ይጠንቀቁ

ምድጃ ከፍተኛ የሆነ በቤት ውስጥ ለሚከሰት እሳት አደጋ መንስኤ ነው፡፡ አንድን መጥበሻ ምድጃ ላይ ጥዶ መርሳት ወይም ምግብ በማብሰል ላይ እያሉ መተኛት ቀላል ነው፡፡ መጥበሻዎን ወይም ድስትዎን በማብሰል ላይ እያሉ ትቶ ያለመሄድ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ተወያዩበት፡፡

ከፍተኛ አደጋ የሚያመጣውን ሁኔታ ለመለየት ይሞክሩ፡፡ ከምድጃ በተለየ ሌላ አማራጮችን መጠቆም ይችላሉ? እንዲሁም የምድጃ መከላከያ መገጠሙን ያረጋግጡ፡፡ ይህ መከላከያ የምድጃው ማናቸውም ቀለበቶች ከልክ በላይ ሲግሉ በራስሰር ያጠፋቸዋል፡፡ ምድጃን ባዶውን ከመቃጠል ወይም ከመጋል ያድነዋል፡፡ እንዲሁም ሌሎች ወደ እሳት አደጋ የሚዳርጉ አጋጣሚዎችን ያስቆማል፡፡

የምድጃ ጓንቶች፣ ፎጣዎች፣ ጋዜጣዎች እና ሌሎች ከምድጃ ጋር በቅርብ የሚቀመጡ እቃዎች በቀላሉ በእሳት በመያያዝ እሳቱም በፍጥነት ወደተለያዩ ቦታዎች ይዛመታል፡፡ ቅባታማ ከሆነ የናፋስ ማራገቢያ ጋር የተገናኘ ነበልባል በበለጠ ሁኔታ በፍጥነት ይዛመታል፡፡ ምድጃዎ አከባቢን ስለማጽዳት ይነጋገሩ፡፡

ምድጃን እንደ ማስቀመጫ ከመጠቀም በተለየ ሌላ የማስቀመጫ ቦታ አማራጭ ማግኘት ይችላሉ? ቤተሰቦች ወይም ጓደኞች እንደ አስፈላጊነቱ ተራ በመውሰድ የሚያደርጉት ጭስ ማጣሪያን የማረጋገጥ እና ቦታውን የማጽዳት ሀሳብ ጥሩ እና ጠቃሚ ነው፡፡

## የኤሌክትሪክ እቃዎችን ያጣሩ

ስለ እሳት አደጋ ሲነሳ ምድጃ ዋነኛውን ሚና ቢወስድም ሌሎች የኤሌክቲሪክ እቃዎችም ያለ አግባብ ካልተጠቀምንባቸው እሳት አደጋ ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ ነዋሪው የኤሌክትሪክ ማሞቂያዎችን እና ሌሎች እቃዎችን በጥንቃቄ እየተጠቀመ እንደሆነ ያረጋግጡ፡፡ የኤሌክትሪክ ግድግዳ ማሞቂያ እና ማቀዝቀዣዎች ከተሸፈኑ እና በአቧራ ከተሞሉ በቀላሉ እሳት ሊያስነሱ ይችላሉ፡፡

ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ሀይል የሚጠቀሙ (ከ1 kW በላይ ) በማራዘሚያ መሰኪያዎች መሰካት የለባቸውም፡፡ ማራዘሚያው የመጨናነቅ አደጋ ላይ ስለሚወድቅ በከፍተኛ ግለት እሳት ሊያያዝ ይችላል፡፡

## የጭስ የማስጠንቀቂያ ደውሎችን ያዳምጡ

ቀደም ያለ ማስጠንቀቂያ አንድ ሰው በጊዜ እንዲያመልጥ እድሉን ያሰፋዋል፡፡ መኖሪያ ቤቱ የጭስ ደወል እንደተገጠመለት እና እንደሚሰራም ያረጋግጡ፡፡ ለመኝታ ቤትም ቢሆን ነዋሪው ደውሉን እንደሚሰማ ለማረጋገጥ ሙከራ ያድርጉ፡፡ በወር አንድ ጊዜ ይህ የጭስ ደወል እንደሚሰራ መሞከርዎን  በተጨማሪም በአመት አንድ ጊዜ ባትሪውን መቀየርዎን እንዳይዘነጉ፡፡

የጭስ ደወሉ ከጠፋ እንዴት መውጣት እንዳለብዎም ተወያዩ፡፡ የእሳት አደጋ ጊዜ ቅድመ ተከተሎችንም አንዳንድ ጊዜ ማከናወን ጥሩ ሀሳብ ነው፡፡ ልምምድ ባለሙያ ያደርጋል፤ በተለይም በአደጋ ጊዜያቶች፡፡

## ነዋሪው የእሳት ማጥፊያውን ማንሳት ይችላሉ?

እሳት በሚያጋጥማቸው ወቅት ምን ማድረግ አለባቸው?እቅድ እና ውይይት ነገሮች በእውን ሲከሰቱ ለማስቀም ይጠቅሙናል፡፡ መኖሪያ ቤቱ የእሳት ማጥፊያ እንዳለው እና ነዋሪው ሊጠቀመው እንደሚችለው ያረጋግጡ፡፡ ሁሉም ቤቶች እሳት ማጥፊያ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ እሳት ማጥፊያው በጣም ከባድ ከሆነ ሌሎች አማራጮችን ለምሳሌ ብርድልብስ ወይም ብናኝ የእሳት ማጥፊያዎችን ለመስጠት ይሞክሩ፡፡ ነገር ግን ከሁሉ በላይ ለነዚህ ሰዎች  ከዛ መውጣት ዋናው ነገር እንደሆነ ያስታውሱ፡፡

## ግልጽ የሆኑ ነበልባሎችን ያስወግዱ

ብዙ አምፖል ማቀፊያዎች እና ጌጣጌጦች ለሻማ ማብሪያነት የተሰሩ ናቸው፡፡ ነገር ግን እነዚህ በቀላሉ ወደ ትናንሽ ርችት እሳቶች ሊቀየሩ ይችላሉ፡፡ ስለ ሻማ አደገኛነት በተለይም በቀላሉ በእሳት ሊያያዙ ከሚችሉ እቃዎች ጋር ሲገናኝ እሳት እንደሚፈጥር ይወያዩ፡፡ የሻማ ማብሪያዎችን በተመለከተ የተለያዩ  በባትሪ የሚሰሩ የእሳት አደጋ መከላከያ አማራጮች የሆኑ የጠረጴዛ መብራቶች አሉ፡፡

## የሲጋራ ቁራጮችን ይጠንቀቁ

የሲጋራ ቁራጭ ከፍተኛ የሆነ የእሳት አደጋ ስጋት ነው፡፡ የምታውቁት የሚያጨስ አረጋዊ ካለ በቤት ውስጥ ሲሆኑ እንዴት እና መቼ እንደሚያጨሱ ጠይቋቸው፡፡  ምናልባትም የእሳት አደጋን ለመቀነስ የሚወስዱት እርምጃ ይኖራል፡፡ ለምሳሌ፤ ውጪ ሆኖ ማጨስ እና መኝታ ቤት ውስጥ ሆኖ ከማጨስ ከፍተኛ  የሆነ የአደጋ ተጋላጭነት ልዩነት አለ፡፡ የእሳት አደጋ ብርድልብስ በሲጋራ የሚከሰቱ እሳት አደጋዎችን ለመቀነስ ይረዳል፡፡